ስለ COVID-19 ክትባት ማወቅ የሚገባቹ በሙሉ:

# የክትባት ጥቅም እርስዎን፣ ቤተሰብዎን እና በአካባቢዎ የሚገኙ ሰዎችን ለመከላከል ይረዳል።

## ፈጣን መርጃዎች:

ክትባት ሕይወት ያድናል።



የ COVID-19 ክትባት ጥብቅ የሆኑ የደህንነት ደረጃዎችን አሟልቷል።





ክትባት ሙሉ ሕብረተሰብዎን ይከላከላል።



COVID-19 ክትባት የማርገዝ ብቃት ላይ ሊያደርስ ስለ ሚችለው ተጽእኖ ምንም መረጃ የለም።

የ COVID-19 ክትባት ይዞታ ውስጥ ምንም የሰው ሆነ የእንስሳ ቅሪት ወይም እንቁላል የለውም።



COVID-19 ክትባት ከብዙ አለማቀፋዊ ጥረት በኋላ የተገኘ ነው።



## ያስታውሱ:

- መረጃ ከሚታመን ምንጭ ይውሰዱ።
- ! የእነዚህ ምንጮች ምሳሌ: የ NHS (ሃገራዊ የጤና አገልግሎት)፣ የአለም የጤና ድርጅት (WHO) እና የብሪቲሽ ቀይ መስቀል ድረገጽ።
- ! ስለ COVID-19 ክትባት ለመረዳት ግዜ ወስደው ያንብቡ። ጤንነትዎ ስለሆነ ግዜ ወስደው በጥንቃቄ እና በጥሞና ማንበብ አስፈላጊ ነው።
- ! ሶሻል ሚድያ ላይ ወይም ዋትስአፕ ላይ ማንኛውም እርግጠኛ ያልሆኑበት ነገር ካነበቡ መለስ ብለው ለማንበብ እና የራስዎን ጥናት ለማድረግ ይሞክሩ።
- ! ተግባራችን ሌሎች ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ተጽእኖ ሊያስከትል ይችላል።



# ጠለቅ ያለ መረጃ

## ክትባት:

- በክትባት ምክንያት ዩኬ ውስጥ እና በአለም ዙሪያ በየአመቱ፣ እስከ 3 ሚልዮን ሕይወት ይድናል።
- በክትባት ምክንያት እንደ ፈንጣጣ፣ ፖሊዮ እና መንጋጋ ቆልፍ ያሉ በሽታዎች ጠፍተዋል ወይም በጣም አሳቻ ግዜ ነው የሚከሰቱት።
- ከተከተብን፣ ሌሎች ሊከተቡ የማይችሉ፣ ከእኛ ይልቅ በቀላሉ ለበሽታ ሊጋለጡ የሚችሉትንም ነው የምንከላከለው (ለምሳሌ የታመሙ እና በሽታ የመከላከል አቅማቸው ዝቅተኛ የሆኑ) ።

## የ COVID-19 ክትባት ጥናት:

- ምንም የተዘለለ አሰራር አልነበረም።
- ክትባት በአፋጣኝ ተጠንቶ እንዲመረት የሚያስችሉ ሶስት ነገሮች አሉ፡ በጣም ብዙ የገንዘብ ድጎማ፣ ብዙ ምንጮች እና ብዙ ተመራማሪዎች። የ COVID-19 ክትባት የእነዚህ የሶስቱ ውጤት ነው።

  ይህንን አይነት አለማቀፋዊ ድጋፍ ያገኘ ሌላ ክትባት የለም።
- አለም አንድ ቅድሚያ ብቻ ነበረው – የዚህን ገዳይ ቫይረስ ስርጭት ማስቆም – ስለዚህ በአለም ዙሪያ ካሉ መንግስታት ብዙ ድጎማ ማግኘት ተችሏል።

## የ COVID-19 ክትባት ደህንነት:

- የክትባቱ ደህንነት፣ ጥራት እና ውጤታማነት አጠራጣሪ ቢሆን ኖሮ በሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎች እንዲከተቡ በፍጹም ፈቃድ አይጸድቅም ነበር።
- ይህ ጥብቅ የሆነ የደረጃ ጥበቃ የወጣው፣ ዩኬ ውስጥ ለጥቅም የሚውሉ መድሃኒቶች በሙሉ ደህንነታቸውን በሚያረጋግጥ፣ በመድሃኒት እና የጤና ጥበቃ ምርት ቁጥጥር ድርጅት ነው።
- ኦክፎርድ /አስትራዜኒካ ክትባት 11,000 ሰዎች ላይ ሙከራ ተደርጎ ነበር። ፋይዘር/ ቢዮንቴክ 43,500 ሰዎች ላይ ሙከራ ተደርጎ ነበር።

## የ COVID-19 ክትባት እንዴት እንደሚሰራ:

- ክትባቱ የሚሰራዉ ወደ ሰውነታችን የበሽታ የመከላከል አቅም ምልክት በመላክ ቫይረሱን የሚዋጋ አንቲቦዲ እንዲፈጠር በማድረግ ነው።
- የእርስዎን DNA አይለውጠውም።
- የማርገዝ ብቃት ላይ ሊያደርስ ስለ ሚችለው ተጽእኖ ምንም መረጃ የለም።

## COVID-19 ክትባት ይዘታዎች:

- ክትባት ይዘታ ውስጥ ምንም የሰው ሆነ የእንስሳ ቅሪት ወይም እንቁላል የለውም።

# እርስዎን እና ቤተሰብዎን ስለ COVID-19 ክትባት በአግባቡ ተረድተው እንዲወስኑ ስለ መርዳት

NHS ስለ COVID-19 ክትባት ታማኝ የሆነ በቅርብ የወጣውን መረጃ ለማኘየት እና በአካባቢዎ ስላለ የክትባት ማዕከል ለማወቅ የሚከተለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ:

ካርዲፍ ኤንድ ቬል ዩኒቨርሲቲ ሄልዝ ቦርድ
cavuhb.nhs.wales/covid-19-mass-vaccination-programme

ስለ ክትባቱ ታማኝ የሆነ በቅርብ የወጣውን መረጃ፣ ስለ ይዘታው፣ ደህንነት እና ሊኖርዎት ስለ ሚችሉ ብዙ ጥያቄዎች ከ 35 ቋንቋዎች በላይ ለማግኘት የሚከተለውን ይጎብኙ:

ዌልስ ሕዝባዊ ጤንነት - phw.nhs.wales/covid-19-vaccination

እዚህ ድረ ገጽ ላይ ያለውን መረጃ በቋንቋዎ ለማንበብ ወይም ለማዳመጥ፣ ድረ ገጹ ላይ ያለውን 'Recite me' የሚለውን ምልክት ይጫኑ።

ከዚህ በፊት ስለ ነበረዎት የጤና ችግር የተወሰነ ጥያቄ ካለዎት እና ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ ወደ ጂፒዎ (የተመዘገቡበት ሓኪም ቤት) ይደውሉ።

06/2021